STAY SAFE MN

# የሃጅ ጉዞ ማረጋገጫ ዝርዝር

ጉዞ አሁንም በ COVID-19 የመያዝ እና የማሰራጨት እድልዎን ይጨምረዋል። **ከታመሙ እና ተመርምረው በ COVID-19 ከተያዙ አይጓዙ።** ይህንን የጉዞ ማረጋገጫ ዝርዝር መመሪያ በመጠቀም ደህንነቱ የተጠበቀ ጉዞ ወደ መካ፣ ሳውዲ አረቢያ ያድርጉ።

## ከጉዞ በፊት

- ከጉዞዎ በፊት ይመርመሩ። **ነጻ** ምርመራ በሶማሊ የማህበረሰብ መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች እና በ Minneapolis/Saint Paul አየር ማረፊያ ማግኘት ይችላሉ።
- የ COVID-19 ክትባቶችዎን፣ ማጠናከሪያዎችን ጨምሮ፣ በጊዜው መውሰድዎን እርግጠኛ ይሁኑ፣ እንዲሁም ሌሎች ከጉዞ በፊት ስለሚያስፈልግዎት ክትባቶች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ። ነጻ የ COVID-19 ክትባቶች በአሜሪካ ማህበረሰብ የክትባት በታ አዳራሽ ላይ ያገኛሉ።
- በሳውዲ አረቢያ አሁን ያሉትን የ COVID-19 መመሪያዎች ይወቁ። [በ COVID-19 መረጃ ላይ (https://sa.usembassy.gov/u-s-citizen-services/covid-19-information/)](https://sa.usembassy.gov/u-s-citizen-services/covid-19-information/) መረጃ ያግኙ።

ማሸግዎን ያረጋግጡ፡-

- [x] የ COVID-19 ፈጣን ምርመራዎች። **ነ፱** ፈጣን ምርመራዎች በሶማሊ የማህበረሰብ መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች ይገኛል።
- [x] በቡድንዎ ውስጥ ለሚጓዙ ለእያንዳንዱ ሰው ከፍተኛ ጥራት ያለው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ።
- [x] የአደጋ ጊዜ አድራሻ መረጃ።
- [x] የ COVID-19 ክትባትዎን ማስረጃ የሚያሳይ የ COVID-19 ክትባት ካርድ ወይም ኤሌክትሮኒክ መረጃ።
- [x] ለጉዞ የሚሆን የእጅ ሳኒታይዘር።

## በጉዞ ጊዜ

- እንደ መስፈርት ባይሆንም፣ CDC በጉዞ ጊዜ ራስዎን እንዲጠብቁ ለመርዳት በአየር መንገድ ውስጥ፣ በአይሮፕላን እና እንደ አዉቶብስ አና ራይድ-ሼር በመሳሰሉ በህዝብ መጓጓዣ ላይ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ እንዲያደርጉ ይመክራል።
- የአፍና አፍንጫ መሸፈኛዎን በመስጊድ እና በሌሎች ማህበራዊ ቦታዎች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ እንዲሁም በሚመከርበት ጊዜ ያድርጉ።
- የህመም ስሜት ሲሰማዎት ወይም ምልክት ሲያዩ፣ የ COVID-19 ፈጣን ምርመራን ይጠቀሙ።
  - ◊ የምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ፣ አይጓዙ፣ የአፍና ያፍንጫ መሸፈኛዎትን ያድርጉ፣ እና የሚያገኙትን ሰው ቁጥር ይመጥኑ።
- ወደ ሚኖሶታ ከመመለስዎ በፊት ምርመራ ያድርጉ። ለአለም አቀፍ ጉዞ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለሚመለሱ የ PCR የ COVID-19 ምርመራ በአየር ማረፊያ ላይ ሊያስፈልግ ይችላል።

## ከጉዞ በኋላ

- ከጉዞ ከሶስት እስከ አምስት ቀን በኋላ የ COVID-19 ምርመራ ያድርጉ። ምልክቶች ማየት ከጀመሩ ቶሎ ይመርመሩ። የ COVID-19 ክትባቶች ላይ ወቅታዊ ካልሆኑ ፣ ከጉዞ በኋላ ለአምስት ቀናቶች በቤትዎ ይቆዩ።
- ማሳሰቢያ፡- በጉዞ ጊዜ ሊታመሙ ወይም በሌሎች በሽታዎች ሊያዙ ይችላሉ። ከታመሙ እና ካልተሻለዎት፣ ወደ ጤና ጣቢያ ይሂዱ እና ለጤና እንክብካቤ አቅራቢው በቅርብ ወደ ሳውዲ አረቢያ መጓዝዎን ያሳውቁ። በሳውድ አረቢያ የሚታወቁ ሌሎች እንደ የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ ሲንድረም (MERS) ያሉ በብዛት የሚከሰቱ በሽታዎችን መመርመር ያስፈልግዎት እንደሆነ ለማወቅ ይረዳሉ።

MINNESOTA

Minnesota Department of Health | health.mn.gov | 625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975 | 651-201-5000
ተለዋጭ ቅርጸት ለመጠየቅ health.communications@state.mn.us ን ያነጋግሩ። (Amahric)

6/21/2022